በኢፌዴሪ የሥራ እና ክህሎት ሚኒስቴር

# የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስቲትዩት የ2014 ዓ.ም የአንደኛ ሩብ ዓመት እቅድ አፈፃፀም

ህዳር 2014

**አዲስ አበባ**

መግቢያ

የ2014 በጀት ዓመት የአንደኛ ሩብ ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቱ የዝግጅት ምዕራፍ ስራዎችን አፈፃፀም የያዘና በአበይት ተግባራት ታቅደው የተሰሩና እየተሰሩ ያሉ ስራዎችን ያካተተ ሲሆን በሀገር ደረጃ በተፈጠረዉ የጸጥታ ችግር ፣ የኮቪድ 19 ወረርሽኝና በሌሎች ምክንያቶች በተፈለገዉ ፍጥነት ያልተፈፀሙ ተግባራት ቢኖሩም ላለፉት 3 ወራት ሲከናወኑ የቆዩና በአሁኑ ወቅትም በመከናወን ሂደት ላይ ያሉ ስራዎችን ያካተተ ነው።

## ርዕይ ተልዕኮ እና እሴቶች

### 1.1 ተልዕኮ

- ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴክኒክና ሙ.ያ መምህራንና ቴክኒሺያኖችን እንዲሁም የአመራር አካላትን በቅድመ ምረቃና በድህረ ምረቃ እንዲሁም ሌሎች ተጨማሪ አጫጭር ስልጠናዎችን በመስጠት ማብቃት
- የአገሪቱን ኢንዱስትሪ በተለይም የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማትን ምርታማነትና ተወዳዳሪነት የሚያጎለብት በጥናትና ምርምር የተደገፉ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስራዎችን መተግበር
- ዉጤታማ የምርምር ስራዎችን በማካሄድ ዉጤት ተኮር የስልጠና ስርዓትን መደገፍ

### 1.2 ርዕይ

- ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የቴክኒክና ሙ.ያ ትምህርት ስልጠና መምህራንና አመራሮችን የሚያፈራ ኢንስቲትዩት በ2017 ዓ.ም ተፈጥሮ ማየት

### 1.3 እሴቶች

ሀ. ለለውጥ ዝግጁነት (Initiative for change)

ለ. ቁርጠኝነት (Committement)

ሐ. ፈጣሪነት (Innovativeness)

መ. ብቃት (Competence)

ሠ. የቡድን መንፈስ (Team sprit)

ረ. ማህበራዊ ኃላፊነት (Social responsibility)

ሰ. ብዝሃነትን ማስተናገድ (Accept diversity)

1. የዝግጅት ምዕራፍ ተግባራት አፈጻጸም፤

## 1.1. ዕቅድ ዝግጅትን በተመለከተ

የ2014 ዓ.ም የዝግጅት ምዕራፍ ዕቅድ ተዘጋጅቶ በዕቅዱም መሰረት ወደ ስራ ተገብቷል፤ ዕቅዱ ሁሉን ያማከለ እና ወጥ በሆነ መንገድ ለማቀድ እንዲቻል ሁሉም ዳይሬክቶሬቶች ዉይይት ተደርጎበት የጋራ ግንዛቤ ከተወሰደ በኋላ እንደየ ዳይሬክቶሬቱ የስራ ባህሪ ዕቅዶች እንዲታቀዱ ድራፍት እቅድ ለዘርፍ ወርዷል ፡፡

## 1.2. አመራርና ፈፃሚ ማዘጋጀት

በተቋም ደረጃ በተዘጋጀው የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ በተቋሙ አመራር ውይይት ተደርጎ እንዲዳብር ለዘርፍ የወረደ ሲሆን ዕቅዱ ተግባራዊ በሚደረግበትና በሚመራበት አግባብ ላይ ሁሉም የአመራር አካል አስፈላጊውን መረጃ እንዲያገኝ፣ ተመጣጣኝ ግንዛቤ እንዲኖረውና በዕቅዱ ላይም ተገቢው የባለቤትነት ስሜት እንዲፈጠር በማድረግ አመራሩን የማዘጋጀት ስራ ተሰርቷል፡፡

## 1.3. የተቋሙን አሰራርና አደረጃጀት ማዘጋጀት፤

ዕለታዊና ሳምንታዊ ውይይቶች አፈፃፀም በተመለከተ የከፍተኛ አመራሩ በየዕለቱ መደበኛ የግንኙነት ጊዜ በማስቀመጥ የየዕለት አፈፃፀም እየገመገመና አቅጣጫ እያስቀመጠ በመምራት ላይ ሲሆን በተመሳሳይ በየ15 ቀኑ የማኔጅመንት ኮሚቴ ስብሰባ በማድረግ የተግባራትን አፈፃፀም በመገምገምና ቀጣይ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ተግባራት እየተመራ ይገኛል፡፡

## 1.4 የ2014 ዓ.ም ቅበላ ዝግጂት

- የተማሪዎች የምግብ ግበአት አቅርቦት ጨረታ በማዉጣት አሸናፊ ድርጅት በመለየት አዋርድ የተደረገና ዉል ተገብቷል ።

- የ2014 ሰልጣኞች ተቀብሎ አገልግሎት ለመስጠት ዝግጅት ተደርጓል

- የምድረ ግቢ ዉበትና እንክብካቤ እና የጽዳት አገልግሎት ተጫራቾችን በማወዳደር ሰነዱ ለአጽዳቂ ኮሚቴ ቀርቧል፣

- በጂማ፣ በእንጦጦ፣የካ ተራራ፣ በዋናውግቢ እና በሳታላይት ኮሌጆች ከ4000 በላይ የችግኝ ተከላ ፕሮግራም በማካሄድ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ተግባራዊ የአድርገናል።

## 2. ዋና ዋና ተግባራት አፈፃፀም

### ግብ 1 ፡- የትምህርትና ስልጠና ጥራትና አግባብነትን ማሻሻል፤

- የስልጠና ግብዓቶችና ስታንዳርዶችን በማሟላት ተገቢውን ስልጠና ተሰጥቷል።
- በኮቪድ ምክንያት ያልተሸፈኑ ኮርሶችን ፕሮግራም በማመቻቸት በብሎክና በክረምት ስልጠና በመስጠት ችግሩን በቀነስ ተችሏል።
- ስልጠናውን በተግባር በማስደገፍ ኢንዳስትሪ የሚያስፈልጋቸውን ኢንዳስትሪ እንዲሔዱና ምልከታ እንዲያደርጉ ተደርጓል።
- የመምህራን የካሪኩለም ዝግጅት አጭር ስልጠና በመስጠት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡
    - የኮርስ ዓውት ላይን ማሻሻያ ተሰርቷል፡፡
    - የሞጁል አዘጋጅ መምህራን ተመድበው ወደ ስራ ገብቷል፡፡
    - የመፅሐፍ ( text book ) አዘጋጅ መምህራን የተመደቡ መሆኑ ፣
- በቴክስታይልና አፓረል ቴክኖሎጂ 12 የLaboratory standard and workshop Guideline ተዘጋጅቷል፡፡
- የስልጠና ፕሮግራሞች አግባባብነትና ጥራት ለማረጋገጥ ሃገራዊ የገቢያ ተኮር ጥናት ተሰርቷል፡፡

### ግብ 2 ፡- የትምህርትና ስልጠና ፍትሀዊነትና ተደራሽነትን ማሳደግ፤

- በቴክኒክና ሙያ ስልጠና ኢንስትትዩት ከ400 ውጤት በላይ ያላቸውን ተማሪዎች ከሁሉም ሀገሪቱ ክፍሎች በቁጥር ከ1000 በላይ በዋናው እና በሳተላይት ግቢዎች

እንዲመዘገቡ ተደርጓል ፡፡ የመግቢያ ፈተና በማቲማቲክስ፣በእንግሊዝኛ፣በፊዚክስ፣ እና በኬሚስትሪ እንዲወስዱ ተደርጓል፡፡

- የመግቢያ ፈተና ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል ከፍተኛ ውጤት ያመጡ 450 ተማሪዎች ተመልምለው እንዲመዘገቡ ተደርጓል፡፡
- በመጀመሪያ ዲግሪ ለኢንድስትሪ ቴክኒሺያን 861 አዲስ ሰልጣኞች ቅበላ ተደርጓል ፡፡ በሳተላይት ኮሌጆች ወንድ=348, ሴት=91፣ድምር፣439 በመደበኛ ፕሮግራም እንዲጨርሱ ተደርጓል፡፡
- በዋናው ግቢ ወንድ፣218 ሴት፣100 ድምር 318 ተማሪዎች በመጀመሪያ እና በሁለተኛዲግሪ ወንድ፣228 እና ሴት፣24 ድምር 252 ተማሪዎች በክረምት እንዲ ጨርሱተ ደርጓል።

**ግብ 3 ፡- ተቋማዊ አቅምና ብቃት (Institutional Capacity) ማጎልበት፣**

- ከ mopede ፕሮጀክት ጋር በመተባበር 5 ሳተላይት ኮሌጅ አሰልጣኞች e-learning ስልጠና ተሰጥቷል ፡፡
- ኢንስትዩት የፈፃሚዎችን አቅም ለመገንባት ለ3 ሰራኞች ትምህርት ዕድሉ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡
- በብየዳ ስልጠና 12 አሰልጣኞች የስነ ስልጠናና ካሪኩለም ዝግጅት ስልጠና ተሰቷል።
- ለሌዘር ቴክኖሎጂ ለ75 የጥቃቅንና አነስተኛ የሌዘር ማህበራት ባለሙያዎችየሶስት ሳምንት ስልጠና መሰጠቱ እና ለ 25 የቴክኒክና ሙያ ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት አሰልጣኞች የ10 ቀን የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡
- በማኑፋክቸሪንግ ት/ት ክፍል ለ50 የቴ/ክ/ሙ/ስ ኮሌጆች መምህራን የአቅም ግንባታስልጠና ተሰጥቷል
- በቲቨት ፔዳጎጂ የማሰልጠን ክህሎት ለ100 የቴ/ሙ/ት/ሥ መምህራን እና ለ25 የኢንዳትሪ ባለሙያዎች የማሰልጠን ክህሎት ስልጠና መሰጠቱ

*ግብ 4- የምርምር፤ፈጠራና ቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ፤*

- *የቴ/ሙ/ስልጠና የተቋማት ዞኒንግ ጥናት ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ የተክኒክና ሙያ ተቋማትን በተልእኮ ለመለየት ከ5 ክልሎችና ሁለት ከተማ አስተዳደሮች መረጃ ተሰብስቦ እየተተነተነ ይገኛል፡፡*
- *17 የምርምር ፕሮፖዛል ጸድቆ በዝግጅት ላይ ይገናል። በ2013 ዓ.ም የተሰሩ ቴክኖሎጂዎችን (plasma cutting machine, plate cutting machine…) የማጠናቀቅ ስራ ተሰርተዋል፡፡*
- *Harvesting machine technology ስራ የማስቀጠል እና ወደ 75 ማድረስ ተችለዋል፡ የTeaching factory concept not ተዘጋጇቷል ።*

*ግብ 5 ፡- የተቋማት ትስስርና የማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎትን ማሻሻል፤*

- *በጥቅሉ 2.5 ሚሊዬን ብር የሚያወጣ እርዳታ ገቢ ወጪ ሆኖ ለተጎጂዎች እንዲደርስ ተደርጓል፡፡*
- *ከተቋሙ አመራርና ሰራተኞች የአንድ ወር ደመወዛቸውን 100% ለመክላከያ በለገሱት መሰረት ከነሀሴ ወር 2013ዓ.ም ጀምሮ በየወሩ291 ሺ.ህ ብር እየተቆረጠ የገኛል*
- *በካዛንቺስ አካባቢ ለሚገኙ አቅመ ደካማ ቤተሰቦች 26 የቤት ዕቃዎች ተሰጥቷል፡፡*
- *ከጂማ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ለመጡ 20 አሰልጣኞች ስልጠና ተሰቷል*
- *ከኢትዮ ኢንጂነሪንግ ግሩፕ ለመጡ 36 ባለሞያዎች ስልጠና ተሰቷል*
- *12 ኢንዱስትሪዎች በባለሙያ እንድጎበኙ ተደርጎ ኢንዱስትሪዎቹም ግንኙነትን ለማጠናከር ተቋሙን እንድጎበኙ ተጋብዘዋል።*
- *ለ10(አስረ) መምህራን ከአምስት ሳተላይት የተውጣጡ እና ለአምስት የዘርፍ አመራር ከ GIZ ጋር በመተባበር በኬንያ ሀገር Earned ፕሮጀክት የአቅም ግንባታ ተሞክሮ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡*
- *የመምህራን የተግባር ስልጠና ክህሎት ለማሳደግ ለ8(ስምንት) መምህራን(አራት ከሌዘር 'አራት ከማኑፋክቸሪንግ)የኢንዱስትሪ ቁርኝት(Attachment) ለአንድ ወር ያህል ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡*
- ከታንዛንያ ሃገር የመጡ መምህራን በሁለት ዙር በተቋምና በኢንዳስትሪ ለአራት መምህራን ለአንድ ወር የሚቆይ የተግባር ተኮር ከGIZ step II **ኘሮግራም በመተባበር** ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ግብ 6 ፡- የሳይንስ ባህል ግንባታ እና የሀገር በቀል እውቀት አስተዳደር ስርዓትን ማጎልበትና መጠቀም፤

---------

## ግብ 7 ፡- የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና አለም አቀፍ አጋርነትን ማሻሻል

- በወርልድ ባንክ ለሌዘርና ለማኑፋክቸሪንግ ዲፓርትመንት የስልጠና ዕቃዎች 14 ዓይነት ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋቸው 198,935.00 ተገዝተው ገቢ ተደርገዋል፡፡
- በወርልድ ባንክለ ተገዛ 1 መኪና የተለየዩ መለዋወጫ ዕቃዎች ተገዝተው ገቢ.ተደርጓል፡፡
- ኮይካ ከተባለ ድርጅት በስጦታ መልክ የተገኘ ማክስበ ቁጥር 17750 እና ሳኒታይዘር 3000 ገቢሆኖ ለሠራተኛው ተከፋፍሎአል፡፡

ግብ 8፡- የመሰረተ ልማት፣ግብአትና ዲጂታል ቴክኖሎጂ ማሳደግ ፤

8.1. ፊዚካል መሰረተ ልማት

- የሰልጣኞች ማደሪያ፣ የስልጠናና አስተዳደር ህንፃ ግንባታ የማጠናቀቅ ስራ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል ፡



- በአጠቃላይ የመብራት መቆራረጥ እንዳይኖርና መብራት ከዋናው መስመር ሲጠፋ የጀኔሬተር አገልግሎት እንዲኖር ተደርጓል፡፡
- በሰልጣኞች ማደሪያና በሌሎች ህንጻዎች የውሃ እጥረት እንዳይኖር አስፈላጊው ክትትል ተደርጓል፡፡
- ብዛታቸው 35 የሆኑ የተደፈኑ የፍሳሽ ማስወገጃ ማንሆሎች ጥገና ተደርጎላቸው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደረጓል፡፡
- በመብራት ሃይል ጊቢ ውስጥ ሁለት የተማሪዎች ማደርያ ህንፃ ላይ የፅዳት ሰራተኞች በመመደብ የፅዳት አገልገሎት ተሰጥቷል ።
- በመማሪያ ህንፃዎች የተሰበሩ የፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች አስፋልት በመቆፈር የተሰበረውን መስመር በአዲስ በመቀየር ፍሳሹ እንዲቆም ተደርጓል
- የዩኒቨርሲቲው የ2013 በጀት ዓመት ዓመታዊ አላቂና ቋሚ የንብረት ቆጠራ ተካናውኗል፡፡

## 8.2 የአይ.ሲ.ቲ መሰረተ ልማትዝርጋታና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሻሻል

- የዲጂታል ሳይኔጅ/ኮንቴንት ማኔጅመንት ሲስተም ሶፍትዌር ማበልፀግና ስራ ሲስተሙ ለምቶ ስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡
- በመጀመሪያው ምእራፍ የተሟሉ ኢኮቴ መሰረተ ልማት አገልግሎቶች አጠናክሮ ማስቀጠል፣ በዚህም የዳታ ሴንተር እና ሙሉ ፋሲሊቲ፤ደረጃውን የጠበቀ የግቢው ኔትወርክ ፤ ለላይብረሪ Digitization ቨርቹዋል ዴስክቶፕ ኢንፍራስትራክቸር፤ የደህንነት ጥበቃ ካሜራ የግቢ ሙሉ ዋን ካርድ አገልግሎት፤የመግቢያ በር ፤ ለህንፃ ውስጥ የማስታወቂያ ማሳያ ዲጂታል ሳይኔጅ
- በሁለተኛው ምእራፍ የሚያገለግሉ ቁሳቁስ ወደ ኢንስቲትዩቱ ገቢ ማድረግ፣ በዚህም ለዳታ ሴንተር ማስፋፊያ የሚውሉ ሰርቨሮች፣ የቪዲዩ ስቶሬጅ፣ ፋየርዎል እና ኮር ስዊች ፤ተጨማሪ የደህንነት ጥበቃ ካሜራዎች (በቁጥር 100)፤ ለ2 ኮንፈረንስ ክፍሎች የሚሆን ዘመናዊ የስብሰባ ሲስተም ፤ ለ2 የመማሪያ ወይም ልዩ ክፍሎች የሚሆኑ ስማርት ክፍል ሲስተም፤ 200 የሆኑ ለቨርቹዋል ዴስክቶፕ ኢንፍራስትራክቸር የሚያገለግሉ ኮምፒተሮች (ላይብረሪ፣ አይሲቲ እና ኤሌክቲካል ትምህርት ክፍሎች ላብራቶሪዎች ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ)፤ በግቢው ውስጥ የሚተከል ግዙፍ ዲጂታል የማስታወቂያ ሰሌዳ ፤ 1 ዘመናዊ የላይብረሪ መፅሃፍት ሮቦቲክ ስካነሮች፣1 ዘመናዊ ሮቦቲክ ስካነር ለሰውሀብት አስተዳደርና ፋይናንስ መረጃ ዲጂታይዜሽን፤
- ለዳታ ማእከሉ የሚያገለግል 250 ኪሎ ቮልት አወር ጀነሬተር አብዛኛው ቁሳቁስ ወደ ግቢው የገባ ሲሆን የተቀሩት በመርከብ ጉዞ ላይ ናቸው፡፡
- የሁለተኛው ምእራፍ ማስፋፊያ ስራም በጅማሬ ላይ ነው፡፡

**ግብ 9፡- የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሻሻል፣**

- ለሩብ አመቱ የተፈቀደው በጀት ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የማድረግ ስራ በሁሉም ፕሮግራሞች ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ይገኛል ፡፡አፈጻጸሙም 33.2% ሆኗል።

ግብ 10፡- የተቋማዊ ለውጥ፣ ዘርፈብዙ ጉዳዮች እና አገልግሎት አሰጣጥ ስራዎችን ማሻሻል፣

**በክረምት**

- የ2009 ወ 306 ሴ 114 ድ420
- የ2010 ወ 268 ሴ83 ድ351
- የ 2011 ወ423 ሴ147 ድ570

  ድምር ወ= 997 ሴ= 344 ድ= 1341

- የ2012 የገቡና በኮቪድ ምክንያት የቋረጡ መደበኛወ 496ሴ184 ድ 680
- ሌደርሽፕ ማስተርስ ወ 50 ሴ 5 ድ55
  - አጠቃላይ ወ= 1543 ሴ= 533 ድ= 2076 ሰልጣኞች በክረምት ከግቢያችን በተጨማሪ ከኢትዮጵያ መብራት ኃይል ትብብር በመጠየቅ ሙሉ አገልግሎት ተሰጥቷል።
  - በጸጥታ ችግር ምክንያት ወደ መጡበት መመለስ ላልቻሉ 65 ሰልጣኞችም አገልግሎት ተሰጥቷል።

ግብ 11፦ የድጋፍ፣ ክትትልና መረጃ ስርዓትን ማሻሻል፣

- 12 የሳተላይት ኮሌጆችን ክትትልና ድጋፍ ስራ ተሰርቷል።
- መረጃዎች በሶኒክ፣ በዲጂታል ሳይኔጅ ፣ሶኒክ ስክሪን ፣ በዜና፣ መልክ ፣ በፎቶ ተደግፈው ለደንበኞች ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል፡

## ግብ 1፡- የትምህርትና ስልጠና ጥራትና አግባብነት ማረጋገጥ

| ስትራቴጂካዊ ዓላማ | ውጤት አመላካች ተግባራት | | መለኪያ | 1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም % | ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.1 የስልጠና የጥራት ስታንዳርዶችን ማሟላት | ኮመፒተር ላብ፡ ተማሪ ጥምርታ | | ጥምርታ | 1፡2 | 1፡2 | 100 | |
| | የተማሪ መምህር ጥምርታ | ቅድመ ምረቃ | ጥምርታ | 1፡25 | 1:25 | 100 | |
| | | ድህረ ምረቃ | ጥምርታ | 1:25 | 1:25 | 100 | |
| | ቤተ-ሙከራዎችን (Lab/workshop)፡የተማሪ ጥምርታ | | ጥምርታ | 1:25 | 1:25 | 100 | |
| | የሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ መምህራን ምጥጥን | | ጥምርታ | 80፡20 | 88፡12 | 88 | |
| | | | | | | | |
| 1.2 የስልጠና ሂደት የተጠናከረ የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት መተግበር | የተተገበረ ተከታታይነት ያለው የጥራት ማረጋገጫ ስርዓት | | ቁጥር | 2 | 1 | 100 | |
| | የተለዩ ተገቢና ዓለም አቀፋዊ ባህሪ ያላቸው የጥራት ስታንዳርዶች ብዛት | | ቁጥር | 3 | 3 | 100 | |
| | የተተገበሩ የመግቢያና መውጫ ፈተናዎች፣ የብቃት ማረጋገጫ ፈተናዎችንና ሌሎች ስርዓቶች፤ | | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | ተግባረዊ የሆነ ተከታታይ ምዘና | | መቶኛ | 90 | 90 | 100 | |
| 1.3. የሰልጣኞች የማጠናቀቅና ምረቃ ምጣኔ መጨመር | የማጠናቀቅ ምጣኔን ለመጨመር የተደረጉ ድጋፎች | የምክር አገልግሎት(አካዳሚክ አድቫይዚንግ | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 1.4 የትምህርትና የስልጠና ብቃት እንዲጠናከር ማድረግ፣ | ከአለም አቀፍ ኢ.ኮ.ቴ ትምህርት አካዳሚዎች ጋር በተፈጠረ ትብብር የተጀመረ የሰርተፍኬት ስልጠና ፕሮግራም | | በቁጥር | -- | 1 | 50% | የ Huawei Academy ለመጀመር ውል ከካምፓኒው ጋር ውል ተፈራርሟል፣ በቀጣይ መምህራን ሰልጥነው፣ ቁሳቁስ ተሟልቶ ተማሪ መዝግቦ አካዳሚውን ማስጀመር |

## ግብ 2፡- የትምህርትና ስልጠና ተደራሽነትና ፍትሃዊነትን ማሳደግ፤

| ስትራቴጂካዊ ዓላማ | ውጤት አመላካች ተግባራት | | | መለኪያ | 1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም % | ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1. የሰልጣኞችን ወደ ተቋሙ የመግባት ዕድል ማስፋት(በመደበኛ፣ በተከታታይ ትምህርት እና በተከታታይ ትምህርት መርሀ-ግብሮች በቴክኖሎጂ ታግዞ በዋናዉ ግቢና በሳተላይቶች በስፋት እንዲሰጥ ማድረግ) | ያደገ የቅበላ አቅም(አድስ) | በመጀመሪያ ድግሪ | በመደበኛ | ቁጥር | 1879 | 0 | | |
| | | | በተከታታይ ትምህርት | ቁጥር | 700 | 0 | | |
| | | | በክረምት ትምህርት | ቁጥር | 800 | 0 | | |
| | | በሁለተኛ ድግሪ | በመደበኛ | ቁጥር | [redacted] | | | |
| | | | በተከታታይ ትምህርት | ቁጥር | 50 | 81 | 100 | |
| | | | በክረምት ትምህርት | ቁጥር | 50 | 52 | 100 | |
| | | በስፔሽያላይዝ እና ፕራክቲሺነርስ ስልጠናዎች (ላይሰንሲንግ ፕሮግራሞች) | | ቁጥር | 100 | 100 | 55 | 51 |
| | አጠቃላይ የተማሪ/ሰልጣኝ ቁጥር (ተደራሽ የተደረገ) | በመጀመሪያ ድግሪ | በመደበኛ | ቁጥር | 9768 | | | |
| | | | በተከታታይ ትምህርት | ቁጥር | 1166 | 2100 | 100 | |
| | | | በክረምት ትምህርት | ቁጥር | 874 | 1427 | 100 | |
| | | በሁለተኛ ድግሪ | በመደበኛ | ቁጥር | 659 | | | |
| | | | በተከታታይ ትምህርት | ቁጥር | 120 | 124 | 100 | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | በክረምት ትምህርት | ቁጥር | 50 | 52 | 100 | |

## ግብ 3. ተቋማዊ አቅምና ብቃትን ማጎልበት

| ዓላማ | ውጤት አመላካች ተግባራት | | መለኪያ | 1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም % | ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.1የተቋሙን የሰዉ ኃብት ብቃት ማረጋገጥ | የትምህርት ዕድል ያገኙ አስተዳደር ሰራተኞች | በመጀመሪያ ድግሪ | በቁጥር | 3 | 0 | 0 | |
| | | 2ኛ ድግሪ | በቁጥር | 3 | 3 | 100 | |
| | | 3ኛ ድግሪ | በቁጥር | 3 | 0 | 0 | |
| 3.2፡- የዩኒቨርሲቲዉን አመራር ብቃትና ችሎታ ማጎልበት፤ | የአቅም ግንባት ስልጠና ያገኙ የተቋሙ አመራሮች | | በመቶኛ | 96 | 90 | 95 | |
| 3.3፡- የዲጂታል ክህሎትንና የቴክኖሎጂ ተጠቃሚነትን ማሳደግ | በኢንስቲትዩቱ በቴክኖሎጅ ታግዘዉ አገልግሎት የሚሰጡ የስራ ክፍሎች | | በመቶኛ | 100 | 80 | | |
| | በዩኒቨርስቲው አገልግሎት ላይ የዋሉ ዲጂታል ሲስተሞች ላይ ለሰራተኞች የአጠቃቀም ስልጠና መስጠት | | በቁጥር | 1 | 2 | 100 | |
| | ተሻሽሎ በተሰራው የሬጅስትራር ሲስተም መምህራን ውጤት ለማስገባት፣ ተማሪዎችም ውጤት ለማየት መጠቀም | | በመቶኛ | 50 | 40 | 90 | ለተማሪዎች የስልጠና ማኑዋል ሰጥቶ ሲስተሙን እንዲጀምሩ ማድረግ |
| | ለ ዳታ ማዕከል የተጨመሩ ዘመናዊ ሰርቨሮች | | በቁጥር | 2 | 2 | 100 | |

| ግብ 4፥የጥናትና ምርምር፤የፈጠራ እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ማሳደግ፤ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ዋና ዋና ተግባራት | ውጤት አመላካች ተግባራት | መለኪያ | 1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም % | ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች |
| 4.1፡- የምርምር እና የቴክኖሎጂ ፈጠራ ባህልን ማሳደግ፤ | በተቋም ደረጃ የተመሰረተ የጆርናል ስርዓት | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | በጥናትና ምርምረ እና በቴክኖሎጂ ስራዎች ዙሪያ የታተሙ/የተዘጋጁ ካታሎግዎች/ህትመቶች/ | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | በተገኘ ፈንድ የተሰሩ የጥናትና ምርምር እና የቴክኖሎጂ ስራዎች | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | ዞኒንግ |
| | የተሸለ ቴክኖሎጂ ሰርተው እውቅናና ሽልማት ያገኙ ከጠቅላላ ተወዳዳሪዎች | መቶኛ | 1 | 1 | 100 | |
| | ተለይተውና ጎልብተው የተሸጋገሩ በተማሪ የተሰሩ ቴክኖሎጂዎች | ቁጥር | | 0 | | |
| 4.2.የአካዳሚክ እና ምርምር ዘርፎችን ትስስር ማሳደግ | አዲስ ለሚከፈቱ እና በስራ ላይ ያሉ ፕሮግራሞችን አሁናዊ እና የወደፊት የገበያ ፍላጎት እና ተገቢነት ለመለየት የተደረገ የገበያ ጥናት ፡ | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | በካሪኩለም ግብዓት ሊሆኑ የሚችሉ ሃሳቦችን ለማመንጨት፡ የተደረገ የተመረቁ ተማሪዎች ሁኔታ ዳሰሳ ጥናት (tracer study) | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | የቴ. ሙ.ት. ስ ተቋማትን የት/ት ጥራት፡ አግባባነት፡ ፍትሃዊነት እና ተደራሽነትን በተመለከተ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለማቅረብ የተካሄዱ ጥናቶቸን | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.3.የተቀዱ እና የተፈጠሩ ቴክኖሎጂዎችን ለተጠቃሚው ማሸጋገር | የተዘረጋ የአሰራር ስርዓት፤ | | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | የተቀዱ፤የተሸሻሉ እና የተፈጠሩ ቴክኖሎጂዎች | በመምህራን | ቁጥር | 2 | 0 | | |
| | | በባለሙያዎች | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | የተሸጋገሩ ቴክኖሎጂዎች | በመምህራን | ቁጥር | | 0 | | |
| | | በባለሙየዎች | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |

ግብ 5፦ የተቋማትና ኢንዳስትሪ ትስስር እና የማኅበረሰብ አቀፍ አገልግሎትን ማሻሻል፤

| ስትራቴጂካዊ ዓላማ | ውጤት አመላካች ተግባራት | መለኪያ | 1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም % | ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.1 **በተቋሙ እና በኢንዱስትሪ መካከል የሥራ ትስስር መፍጠርና ማጠናከር፣** | በተቋሙና በኢንዱስትሪዎች መካከል የተፈረመ የስምምነት ሰነድ | ቁጥር | 5 | 2 | 45 | |
| | ከኢንዳስትሪዎች ጋር በመሆን የተሰሩ ስራዎች | መቶኛ | | 0 | | |
| | ተቋሙ አግልግሎት ያገኙባቸው ኢንዱስትሪዎች ብዛት ከጠቅላላ ከተፈራረምንባቸው | በቁጥር | 5 | 10 | 100 | ፣ምልከታ፣ ፕሮጀክት ስራ፣ |
| | ከተቋሙ አግልግሎት የተጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች | ቁጥር | 10 | 5 | 50 | |
| 5.3.የምርምርና ቴክኖሎጂ ስራዎች የማህበረሰቡን ችግር እንዲፈቱ ማስቻል | የተለያዩ የዳሰሳ ጥናቶችን በማካሄድ የተለዩ የማህበረሰብ ችግሮች፤ | ቁጥር | 1 | | | |
| | በማህበረሰብ ድጋፍ ተጠቃሚ የሆኑ ሰዎች | ቁጥር | 50 | | 100 | |
| | የማህበረሰብ አገልግሎት ስራ ውስጥ የተሳተፈ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ብዛት ከጠቅላላ | መቶኛ | 10 | | 100 | |
| | የማህበረሰብ አግልግሎት ስራ ውስጥ የተሳተፉ የአከባቢው ሰዎች ብዛት | ቁጥር | 20 | | 100 | |

## ግብ 6፦ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎና አለም አቀፍ አጋርነት ማሻሻል

| ዓላማ | ውጤት አመላካች ተግባራት | መለኪያ | 1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም % | ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 6.1 የባለድርሻ ተሳትፎን ማሳደግ | የባለድርሻ አካላት ጋር ተቀርጾ የተተገበረ ፕሮጀክት | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | ተማሪዎች/ሰልጣኞች በተግባር የተደገፈ ትምህርትና ስልጠና እንዲወስዱና ለሙያቸው ብቁ ሆነው እንዲዘጋጁ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በየጊዜው የተደረገ ግምገማ | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በትብብር የተሰጡ አጫጭር ስልጠናዎች | ቁጥር | 50 | 116ፔዳ | 100 | |
| 6.2 አጋር አካላት ተሳትፎን ማሳደግ | የተሳተፉ አገር ውስጥ ያሉ ዓለም አቀፍ ተቋማትና የልማት አጋር ድርጅቶች | ቁጥር | 2 | 1 | 50 | |
| | ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች የተገኘ ድጋፍ | አይነት | 2 | 2 | 100 | |
| | ከተለያዩ ግብረሰናይ ድርጅቶች የተገኘ ድጋፍ | ብር | 5 | 8ሚሊዮን | 100 | |
| 6.3 ከውጭ ሃገር ተቋማት ጋር ትሥሥር በመፍጠር በጋራ መስራት፤ | በሌሎች ዓለም አቀፍ የምርምር እና የትምህርት ተቋማት በመሄድ ተጠቃሚ የሆኑ ተማሪዎች | ቁጥር | 2 | 0 | 0 | |
| | ወደ ተቋሙ በመምጣት ተጠቃሚ የሆኑ የውጭ አገር ተማሪዎች | ቁጥር | 174 | 100 | 76 | |
| | ወደ ተቓሙ በመምጣት በማሰልጠን ፤ በምርምር፤ እና ቴክኖሎጂ ቅጅ ሂደት የተሳተፉ የውጭ አገር መምህራንና ተመራማሪዎች | ቁጥር | 55 | 44 | 80 | |

| ግብ 7፡- መሰረተ ልማት፣ ግብአት እና ዲጂታል ቴክኖሎጂን ማሳደግ፤ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ስትራቴጂካዊ ዓላማ | ውጤት አመላካች ተግባራት | መለኪያ | 1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም % | ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች |
| 7.1. የማስፋፊያ ግንባታ እና የልህቀት ማዕከላት መሰረተ ልማት ማሟላት፤ | በጥራት የተገነቡ የማስፋፊያ ግንባታዎች ከጠቅላላው | መቶኛ | 100 | 90 | 90 | |
| | የተገነቡ ተጨማሪ ስልጠና በ (Further training) | መቶኛ | 20 | 10 | 50 | |
| | በዋናው ግቢ የተገነቡ የልህቀት ማዕከላት | መቶኛ | 20 | 10 | 50 | |
| | ለቢሮ በሚሆኑ የፓርቲሽን ስራዎች | መቶኛ | 10 | 10 | 100 | |
| | በዲዛይን ማስተር ፕላን መሰረት የተከናወኑ ግንባታዎች | መቶኛ | 100 | - | - | |
| | የተከናወኑ የአጥር እና የፍሳሽ ማስወገጃ ግንባታዎች | በቁጥር | 4 | 2 | 50 | |
| 7.2. ለነባርና አዳዲስ መሰረተ ልማቶች እድሳት እና ጥበቃ በማድረግ በሰረታዊ አገልግሎቶችን ማሟላት | ወቅቱን የጠበቀ ጥገና እና ማሻሻያ የተደረገላቸው ህንጻዎች ከጠቅላላው | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| | ጥገና እና ጥበቃ የተደረገላቸው የመማሪያ ማሺነሪዎች | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| | የተሟሉ የሕንፃ ጥገና /እድሣት የግንባታ ግብአቶች | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 7.3. ለስልጠና፣ ለምርምር እና ለቴክኖሎጂ የሚውሉ ግብአቶችን ማሟላት፤ | የተሟሉ የስልጠና ግብአቶች | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| | የምርምር የመረጃ ቋት የተጠቀሙ ተመራማሪዎች | መቶኛ | 25 | 0 | 0 | አክሰስ ኮድ የለውም |
| | የተደረጉ የመረጃ መተንተኛና መሰብሰቢያ ቴክኖልጂዎች | አይነት | 2 | 2 | 100 | SPSS,STATA |
| | የተሟሉ ቴክኖሎጂን ለመተግበር የሚያስችሉ ግብአቶች | መቶኛ | 25 | 25 | 100 | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | በተገቢው ግብአቶች የተሟሉና የተደራጁ ወርክሾፖች (የቴስቲንግና የፍተሻ መሳሪያ ዝግጁ ማድረግን ጨምሮ) ከጠቅላላ | መቶኛ | 25 | 25 | 100 | |
| | የተሟላ የውሀ እና የመብራት አገልግሎት ያገኙ ህንጻዎች ከጠቅላላው | መቶኛ | 75 | 75 | 100 | |
| 7.4.የአረንጓዴ ዘላቂ ልማትን ማጠናከር፡- | በ Green University ሚናዎችና ጥቅሞች ዙሪያ የተዘረጋ ስርዓት | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | በ Green tvt ታሳቢ ተደርጎ የተገነቡ ግንባታዎች | መቶኛ | 25 | 25 | 100 | |
| | የተፈጠረ ምቹ ፣ ፅዱና ተስማሚ የ ስልጠና እና የስራ አካባቢ | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| 7.5.የዲጂታል ቴክኖሎጂስርዓትንና ውጤቶችን ማሳደግ፡- | የተተገበረ የኢንተርፐራይዝ ካምፓስ ማኔጅመነት ሲስተም | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | በኔትዎርክ የተሳሰራቸው ተቋማትና ድርጅቶች ብዛት | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | የተተገበረ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት ማድረሻ (IT service delivery Platform) ሲስተም | መቶኛ | 25% | 25 | 100 | |
| | የተዘረጋ ዲጂታላይዝድ የሆነ የካምፓስ ደህንነት ሲስተም ከአጠቃላይ | መቶኛ | 60% | 60 | 100 | |

| ግብ 8 ፦ የሀብት አጠቃቀም ዉጤታማነትን ማሳደግ፣ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ስትራቴጂካዊ ዓላማ | ውጤት አመላካች ተግባራት | | መለኪያ | 1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም % | ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች |
| 1. የሀብት አጠቃቀም ውጤታማነትን ማሻሻል | በካይዘን ስርዓት ንብረቶች አደራጅተዉ የያዙ ስራ ክፍሎች፣መማሪያ ክፍሎችና ዎረክ ሾፖች | | በመቶኛ | 40 | 50 | 100 | ማዝለቅ |
| | ተግባራዊ የሆነ የፋይናንስ ግልፀኝነት | መደበኛና ካፒታል | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| | | የፕሮጀክት ሒሳቦች | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| | | ይፋ የተደረጉ የኦዲት ግኝቶች | በቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | | የግዥ አፈፃፀም በግዥ ዘዴና በብር መጠን | መቶኛ | 1 | | 100 | |
| | | ሀብት ያስመዘገቡ ሰራተኞችና አመራር | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| | ለታለመለት አላማ በዉጤታማነት የዋለ በጀት | | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| | በተቀመጠዉ እስታንዳርድ መሰረት የተፈፀመ ግዥ | | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| | በታቀደው ልክ ጥቅም ላይ የዋለ በጀት | | በመቶኛ | 100 | 33.2 | 33 | |

| ግብ 9.የተቋማዊ ለውጥ፣ ዘርፈብዙ ጉዳዮች እና አገልግሎትአሰጣጥ ስራዎችን ማሻሻል፣ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ስትራቴጂካዊ ዓላማ | ውጤት አመላካች ተግባራት | መለኪያ | 1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም % | ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. የለውጥ እና የአገልግሎት አሰጣጥ ስራዎችን ማከናወን፤ | ለስራ ክፍሎችን የተሟላ የሰዉ ኃይል ብዛት | በቁጥር | 635 | 650 | 100 | |
| | የአሰራር ስርዓትን የሚያሻሽልና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የተቋሙ የውስጥ አደረጃጀት | መቶኛ | 70 | 70 | 100 | |
| | የተዘጋጁ/የተከለሱ/የተስተካከሉ አስፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች | በቁጥር | 4 | 1 | 25 | |
| | በተሻሻሉ የተለያዩ ጥቅማጥቅም አሰራር ስርዓቶች ተጠቃሚ የሆኑ ሰራተኞች | በመቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| | በስታንዳርድ መሰረት የተሠጡ አገልግሎቶች | መቶኛ | 100 | 100 | 100 | |
| | የተዘረጋ ዘመናዊ የቅሬታና አቤቱታ ማቅረቢያ ስርዓት | በቁጥር | 3 | 3 | 100 | |
| | ያደገ የተገልጋይ እርካታ | መቶኛ | 80 | 80 | 100 | |

ግብ 10 ፦ የድጋፍ፣ ክትትልና መረጃ ስርዓትን ማሻሻል፣

| ስትራቴጂካዊ ዓላማ | ውጤት አመላካች ተግባራት | መለኪያ | 1ኛ ሩብ ዓመት እቅድ | አፈጻጸም | አፈጻጸም % | ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10.1 የአፈጻጸም ውጤታማነትን ሊያረጋግጥ የሚያስችል የክትትልና ድጋፍ ስርዓትን በተሟላ ሁኔታ መተግበር፤ | ከማኔጅመንት እስከ ስራ ክፍል የተደረገ እቅድ አፈጻጸም ግምገማ | ቁጥር | 2 | 2 | 100 | |
| | የተልዕኮ አፈጻጸምን ሊያረጋግጥ የሚችል የውስጥ ክትትልና ድጋፍ | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |
| | በየደረጃው የተደረገ የሩብ ዓመት፣ የአፈጻጸም ሪፖርትና የተሰጠ ገንቢ ግበረ መልስ | ቁጥር | 1 | 1 | 100 | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | |
| 10.2፡- መረጃ አያያዝና አደረጃጀት ስርዓትን በማሻሻል በቀላሉ ተደራሽ ማድረግ፤ | በጥራት በሶፍትና በሀርድ ኮፒ የተደራጁ መረጃዎች | መቶኛ | 70 | 50 | 77 | |
| | የቀነሰ የመረጃ ችግር | መቶኛ | 5 | 2.5 | 50 | |
| | ለሁሉም ተደራሽ የሆነ የተቋሙ አጠቃላይ መረጃ | መቶኛ | 75 | 75 | 100 | |

# 3. ጠንካራ ጎንና ያጋጠሙ ችግሮች

## 3.1 ጠንካራ ጎን

- የባለፈው በጀት ዓመት እቅድ አፈጻፀም ተገምግሞ የባለድርሻ አካላትን ያሳተፈ አመታዊ ዕቅድ መዘጋጀቱ፣
- አመራሩ፣ ሠራተኛው ከኮሮና ወረርሽኙ ራሳቸውን እየጠበቁ ሥራዎች እንዳይጓተቱ በማድረግ ተገልጋዮች ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኙ ያሳዩት ተነሳሽነትና ቁርጠኝነት፣
- በኮረና ምክንያት ያጋጠመንን የአካዳሚክ ካላንደር መዛነፍ,በክረምት መርሀ ግብር ተጨማሪ አማራጮችን በመጠቀም ማካካስና ችግሩን መቀነስ መቻሉ
- ከባለድርሻ ጋር ያለው የቅንጅትና ትብብር እየተሻሻለ መምጣቱ፣

## 3.2 ያጋጠሙ ችግሮች

- ወቅቱንና ጥራቱን የጠበቀ የስራ አፈጻፀም ሪፖርት አለማግኘት፡
- በተከሰተው ጦሪነት ምክንያት ሠልጣኞች ቅበላ መራዘምና 4 ሳታላይቶችም መዘጋታቸው
- በኮቪድ -19 ወረርሽኝ ምክንያት የአካዳሚክ ካላንደር መዛነፍ,
- የሰልታኞች ማደሪያ ህንጻዎች በጥገና ያልተጠናቀቁ የመስኮት መስታወቶችና የግድግዳ መስኮቶች መኖር